UW Medicine

# የአንጀት ምርመራ (ኮሎኖስኮፒ)

## *ሙቪፕሪፕ(ሆድዕቃ ማፅጃ)ን በመጠቀም መዘጋጀት*

የእርስዎ የኮሎኖስኮፒ (አንጀት ምርመራ) ለ ____________________, ________________________, በ ________ ተቀጥረዋል፡፡
ቀን ዕለት ሰዓት

| **7 ቀናት ቀደም ብሎ** | **5 ቀናት ቀደም ብሎ** | **1 ቀን ቀደም ብሎ** | **በምርመራው ቀን /ዕለት** |
|---|---|---|---|
| ቀን | ቀን | ቀን | ቀን |
| • **የደም ማቅጠኛ መድሃኒት** እንደ ኮሞዲን(ዋርፋሪን) ወይም ፕላቪክስ (ክሎፒዶግሬል) እየወሰዱ ከሆነ፡-<br>– እነኝህን መድሃኒቶች ላዘዘው ዶክተር ይደውሉ<br>– የአንጀት ምርመራ (ኮሎኖስኮፒ ) እንዳለዎት እና ምርመራውን መቸ እንደሚያደርጉ ይግለፁለ(ላ)ት<br>– ለደም ማቅጠኛ መድሃኒትዎ የተለየ መመሪያ ካለ ይጠይቁት<br>• **ቀጠሮን መሰረዝ፡-** የቀጠሮ ቀንዎን መቀየር አለያም መሰረዝ ከፈለጉ በ206__________ ይደውሉ፡፡<br>• **ከሆስፒታል ስንብት እና መጓጓዣ**<br>– ወደቤትዎ ለመመለስ ዝግጁ ሲሆኑ አዋቂ የቤተሰብ ኣባል ወይም ጓደኛ **መሆን አለበት የሚመልስዎት**፡፡ምርመራውን ካጠናቀቁ በኋላ ብቻዎትን ማሽከርከር፤ታክሲ ወይም አዎቶብስ አለያም የሆፒሊንክ ወይም የአካል ጉዳተኛ መጓጓዣን መጠቀም አይችሉም፡፡<br>– **ወደቤት የሚመልስዎት አዋቂ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ አብሮዎት ካልመጣ የምርመራ ቀጠሮዎ የሚሰረዝ ይሆናል፡፡**<br>– በቀሪዎቹ የቀንዎ ሰዓታትም ቤት ውስጥ አብሮዎት የሚሆን ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው እንዲኖር አጥብቀን እንመክራለን፡፡ | • ለውዝ ወይም ፍሬ ያላቸውን ምግቦች ከመመገብ **ይቆጠቡ**<br>• ብረት(አይረን) አለያም ብረትን የያዘ ብዝሃ-ቫይታሚኖችን ከመውሰድ **ይቆጠቡ፡፡**<br>• የታዘዘውን ሙቪፕሪፕን (የሆድዕቃ)ማፅጃ **ይውሰዱ፡፡**<br>• ይህንን መመሪያ በጥንቃቄ **ያንብቱ**<br>• **የስኳር ህመም ካለበዎት**<br>– የስኳር መድሃኒትዎን ለሚከታተለው ሃኪም ይደውሉለት<br>– የአንጀት ምርመራ /ኮሎኖስኮፒ እንዳለበዎት እና ቀኑን ለህክምና አቅራቢዎ ይንገሩት<br>– ለስኳር መድሃኒትዎ የተለየ መመሪያ ካለ ይጠይቁ፡፡ | • ለቁርስ፡- ቀለል ያሉ ክራከሮችን (የተጠበሰ ዳቦ ጥራጥሬ የሌለበት)፣ የበሰለ ሴሪያል(የፋሪና ወይም የስንዴ እልበት፣ግሪትሰ)፤ ቀዝቃዛ ሴሪያል(ኮርን ፍሌክስ፣የሩዝ ኮቸሮ)፣ነጭ ሩዝ፣ኖዱል ወይም ፓስታ<br>• **ጠዋት ላይ** ፡-የሆድዕቃ ማፅጃ ፈሳሽን(ሙቪፕሪፕ)ን ያዘጋጁ፡፡"አንድ እጅ(ፖውች) ኤ" እና "አንድ እጅ (ፓውች) ቢ" በሙሉ ወደ እቃው ይገልብጡ፡፡ እቃው ላይ ባለው መስመር ድረስ ለብ ያለ ውሃ ይጨምሩ፡፡ ከዛ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ስር ያስቀምጡት ፡<br>• **ከ 12 ሰኣት(ቀትር) በኋላ፡**ምንም አይነት ጠጣር ምግብ አይመገቡ፡፡በቀሪው የቀንዎ ግዜ ጥርት ያለ ፈሳሽ እንደ ጭማቂ(ቱፋህ፣ወይን ወይም ክራንቤሪ) አጥሚት፣ጥቁር ቡና ወይም ሻይ፣የስፖርት መጠጦች፣ለስለሳ ወይም ጄላቲን(አረንጓዴ ወይም ቢጫ ብቻ )<br>• **7 p.m ላይ ፡-** በየ 15 ደቂቃዉ 8 አውንስ የየሆድዕቃ ማፅጃ/ሙቪ ፕሪፕን ይጠጡ፡፡ ከዛ በኋላ 32 አውንስ ጥርት ያለ ፈሳሽ ይጠጡ፡፡ ይህ የግድ ተቅማጥ መፍጠር አለበት፡፡ሁለተኛውን እቃ ያዘጋጁ፡፡ፍሪጅ ውስጥም ያኑሩት፡፡ | • ምንም ዓይነት ጠጣር ምግብ አይብሉ፡፡<br>• **ከቀጠሮዎ 5 ሰዓታት ቀደም ብሎ** ፡- የሆድዕቃ ማፅጃ ፈሳሽ(ሙቪፕሪፕ)ን 2ኛ እቃ መጠጣት ይጀምሩ፡፡ በየ 15 ደቂቃ ልዩነት 8 አውንስ ይጠጡ፡፡ ሙቪፕሪፑን ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ ቢያንስ 16 አውንስ የሚሆን ጥርት ያለ ፈሳሽ ይጠጡ፡፡<br>• የሆድዕቃ ማፅጃ(ሙቪፕሪፑን) ከጠጡ ከ 1 ሰዓት በፊት ወይም በኋላ ጠዋት ላይ የሚወስዷቸውን መድኃኒቶች በውሃ ይዋጧቸው፡<br>• ለቀጠሮዎ 2 ሰዓት እስኪቀረው ድረስ ጥርት ያለ ፈሳሽ መጠጣትዎን ይቀጥሉ፡፡<br>• **ቀጠሮዎ 2 ሰዓት ከቀረው ግዜ ጀምሮ** ፡-ምንም ዓይነት ነገር በአፍዎ መውሰድ የለብወትም፡፡<br>**ወደ ቀጠሮዎ ሲመጡ ማምጣት ያለብዎት ነገሮች፡-**<br>• አዋቂ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ<br>• በአሁኑ ወቅት የሚወስዷቸውን ሁሉንም ዓይነት መድሃኒቶች<br>• መታወቂያ፣የኢንሹራንስ ካርድ እና አስፈላጊ ከሆነ የወጭ መጋራት ክፍያ (ኮፔይ)<br>• ከአንጀት ምርመራው በፊት ሁሉንም ጌጣጌጦች ማውለቅ ይኖርበዎታል፡፡ከተቻለ ውድ ውድ እቃዎችዎን ቤት ያስቀምጡ፤አለያም የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛዎ እንዲያስቀምጥልዎ ያድርጉ፡፡ |

## የህክምና ቦታ እና የመኪና ማቆሚያ

**ሃርበርቪው ህክምና ማእከል**
የኢንዶስኮፒ ክፍል
Maleng Building, 8th Floor
410 Ninth Ave., Seattle, WA 98104
**206.744.3519**
የመኪና ማቆሚያ 7 ቀን በሳምንት እና 24 ሰአት በቀን በ 9ኛውና ጀፈርሰን ጋራጅ(P2) ከጄምስ እና ቴሪ ተቃራኒ/ትይዩ

**የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ህክምና ማዕከል**
የምግብ አፈጫጨት ጤና ማዕከል
Surgery Pavilion, 3rd Floor
1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
**206.598.4377**
ከ N.E. Pacific St., ወደ ድንገተኛ ህክምና ክፍል የሚወስደውን አማላካች ይከተሉ፡፡ከላይኛው ጠቋሚ, ወደ Surgery Pavilion Parking Garage በኩል ወደ ግራ ይታጠፉ፡፡መኪናዎትን ካቆሙ በኃለ ወደ 3 ኛው ፎቅ ለመሄድ ሊፍቱን/አሳንሳሩን ይጠቀሙ፡፡ከዛ ወደ ምግብ አፈጫጨት ጤና ማዕከል ለመሄድ ወደ ቀኝ ይታጠፉ፡፡

**ኖርዝ ዌስት ሆስፒታ**
1550 N. 115th St., Seattle, WA 98133
**206.368.1770**
የኢንዶስኮፒ ምርመራ ክፍል የሚገኘው ከዋናው ሆስፒታል በመጀመሪያው ፎቅ ላይ ስታር ባክስን ተሻግሮ ነው፡፡

**ኢስትሳይድ ስፔሻሊስቶች ማዕከል**
3100 Northup Way, Bellevue, WA 98004
**425.646.7777**
Free parking on site.

**ሲያትል ካንሰር ኬር አሊያንስ**
825 Eastlake Ave. E., Seattle, WA 98109-1023
**206.606.1329**
ምርመራ ክፍሉ የሚገኘው በክሊኒኩ 2ኛ ፎቅ ላይ ነው፡፡

# ልዩ መመሪያዎች

- **የስኳር ህመም መድኃኒት የሚወስዱ ከሆነ** ፡የአንጀት ምርመራ /ኮሎኖስኮፒ በሚደረግበት ቀን እና ከዛ ግዜ ቀደም ብሎ ላለው ቀን መድሃኒትዎ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ በነኝህ 2 ቀናት ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለበዎት የስኳር ህመም ህክምና አቅራቢዎች ጋር ይወያዩ፡፡
- **የሆድ ድርቀት ካለበዎት አለያም የህመም ማስታገሻ በየቀኑ የሚወስዱ ከሆነ**
  - 1 ጠርሙስ ማግንዥየም ሲትሬት ከመድሃኒት መደብርይግዙ፡፡
  - ለምርመራው 2 ሙሉ ቀናት ሲቀሩት ማታ 8 p.m ላይ ሙሉ ብልቃጡን ይጠጡት፡፡

## ኮሎኖስኮፒ ምንድነው?

*ኮሎኖስኮፒ ዶክተርዎ የትልቁ አንጀት ውሰጣዊ ንጣፍን እንዲያይ የሚያስችል ምርመራ ነው፡፡*

## ምን ሊከሰት እንደሚችል መጠበቅ ያለበዎት

በክርንዎ ደም ስር(ቬይን) ላይ በተተከለው የምግብ መርፌ አማካኝነት ሰመመን ውስጥ የሚከት መድሃኒት ይሰጠዎታል፡፡ ኣብዛኛዎቹ ታካሚዎች በዚህ ወቅት ይተኛሉ፡፡እርስዎ ካልተኙ እና የምቾት ስሜት ካልተሰማዎት እባክዎን ይደውሉሉን፡፡ ምቾት እንዲሰማዎት የተቻለንን እናደርጋለን፡፡

ዶክተርዎ ተጣጣፊ የሆነ ቱቦ በፊንጢጣዎ ውስጥ ይከታል፡፡ የቱቦው መጠን የእጅ ጣትን ያክላል፡፡ዶክተርዎ የህብረ-ህዋስ ናሙና ሊወስድ ይችላል፤ አለያም እብጠቶችን ቆርጦ ሊያስወግድ ይችላል፡፡

የአንጀት ምርመራው /ኮሎኖስኮፒ ከ 30-45 ደቂቃ ይፈጃል፡፡ ነገር ግን ለዝግጅት እና ከህክምና በኃላ ለማገገም ሲባል ቀጠሮዎ ረጅም ግዜ ሊወስድ ይችላል፡፡

ከዛ በኃላ የእርስዎ ዶ/ር ስለ ውጤቱ ሊነግርዎት ይችላል፡፡ ውጤቱ ወዲያውኑ ካልደረሰ መቸ ሊጠናቀቅ እና ሊደርስዎት እንደሚችል እናሳውቀዎታለን፡፡

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎቻችሁ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው ፡፡እባክዎን ጥያቄ ወይም ሀሳብ ካለዎት ይደውሉሉን፡፡ በስራ ቀናት ከ 8 a.m እስከ 5 p.m ፤ የኮሎኖስኮፒ ምርመራ ቀጠሮ ወደታያዘበት ክሊኒክ ይደውሉ፡፡ ከስራ ቀናት/ሰዓት ውጭ፣ ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓላት ቀናት ሃርበርቪው የሚገኘውን የማህበረሰብ ክብካቤን በ 206.744.2500 ይደውሉ፡፡

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2012, 2015, 2016, 2018
Clinician Review: 03/2018
AMHARIC translation by HMC Interpreter Services
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

UW Medicine

# Colonoscopy

*How to prepare with MoviPrep*

Your colonoscopy is scheduled for ________________, ____________________, at _______
DAY DATE TIME

| 7 Days Before | 5 Days Before | 1 Day Before | On Procedure Day |
|---|---|---|---|
| Date: | Date: | Date: | Date: |
| • **If you take blood-thinning medicines** such as Coumadin (warfarin) or Plavix (clopidogrel):<br>– Call the doctor who prescribed these medicines.<br>– Tell the doctor you are having a colonoscopy, and the date of your procedure.<br>– Ask for special instructions for your blood-thinning medicines.<br>• **Cancellations:** If you need to reschedule or cancel your test, call 206.____________.<br>• **Discharge and transportation:**<br>– An adult family member or friend **must** pick you up when you are ready to go home. You cannot drive, take a bus or taxi, or use a service such as Hopelink or Paratransit by yourself after your test.<br>– **Your test will be cancelled if you do not have an adult family member or friend to take you home.**<br>– We strongly advise that a responsible adult stay with you for the rest of the day. | • **Stop** eating foods that contain nuts or seeds.<br>• **Stop** taking iron and any multivitamin that contains iron.<br>• **Fill** your MoviPrep prescription.<br>• **Read** this handout carefully.<br>• **If you have diabetes:**<br>– Call the provider who manages your diabetes medicines.<br>– Tell the provider that you are having a colonoscopy and the date of your procedure.<br>– Ask for special instructions for your diabetes medicines. | • **For breakfast:** You can eat plain crackers (saltines or Melba toast, no seeds), cooked cereals (farina, cream of wheat, grits), cold cereal (corn flakes, puffed rice), white rice, noodles, or pasta.<br>• **In the morning:** Prepare the MoviPrep solution. Empty one "Pouch A" and one "Pouch B" into the container. Add lukewarm water to the top line of the container. Store in the refrigerator.<br>• **After 12 noon:** Do not eat any solid food. For the rest of the day, drink clear liquids such as juice (apple, grape, or cranberry), broth, black coffee or tea, sports drinks, soda, or gelatin (green or yellow only).<br>• **At 7 p.m.:** Drink 8 ounces of MoviPrep every 15 minutes. Then drink at least 32 ounces of clear liquid. It should cause diarrhea. Prepare the 2nd container. Store it in the refrigerator. | • **Do not eat any solid food**.<br>• **5 hours before your appointment**: Start drinking the 2nd container of MoviPrep. Drink 8 ounces every 15 minutes. After you have finished the MoviPrep, drink at least 16 ounces of a clear liquid.<br>• 1 hour before or after drinking the Moviprep, take your morning medicines with water.<br>• Keep drinking clear liquids until 2 hours before your appointment.<br>• **Starting 2 hours before your appointment:** Do not take anything by mouth.<br>**What to bring to your appointment:**<br>• An adult family member or friend<br>• A list of all medicines you currently take<br>• Photo ID, insurance card, and co-pay, if needed<br>• You will need to remove all jewelry and piercings before your colonoscopy. If you can, leave all valuables at home, or give them to your family member or friend for safekeeping. |

## Locations and Parking

**Harborview Medical Center**
GI Endoscopy Suite
Maleng Building, 8th Floor
410 Ninth Ave., Seattle, WA 98104
**206.744.3519**
Parking 24 hours a day, 7 days a week in the Ninth and Jefferson Garage (P2) off James and Terry.

**University of Washington Medical Center**
Digestive Health Center
Surgery Pavilion, 3rd Floor
1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
**206.598.4377**
From N.E. Pacific St., follow signs to the Emergency Room. At the stop sign, turn left into the Surgery Pavilion Parking Garage. After parking, take the elevator to the 3rd floor. Turn right into the Digestive Health Center.

**Northwest Hospital**
1550 N. 115th St., Seattle, WA 98133
**206.368.1770**
The Endoscopy Procedure Suite is on the 1st floor of the main hospital, across from Starbucks.

**Eastside Specialty Center**
3100 Northup Way, Bellevue, WA 98004
**425.646.7777**
Free parking on site.

**Seattle Cancer Care Alliance**
825 Eastlake Ave. E., Seattle, WA 98109-1023
**206.606.1329**
The Procedure Suite is on the 2nd floor of the clinic.

## Special Instructions

- **If you take medicines for diabetes**: Your medicines will need to be adjusted for the day before and the day of your colonoscopy. Talk with your diabetes care provider about what to do on these 2 days.
- **If you have severe constipation or are taking pain medicine every day:**
  - Buy a bottle of Magnesium Citrate at a drugstore.
  - 2 days before your procedure, at 8 p.m., drink the full bottle.

## What is a colonoscopy?

A *colonoscopy* allows your doctor to look at the lining of your large intestine.

## What to Expect

You will receive a *sedative* (medicine to help you relax) through an *intravenous line* (IV) placed in your vein. Most patients fall asleep. If you do not fall asleep and feel some discomfort, please tell us. We will do our best to help you be comfortable.

Your doctor will place a flexible tube into your rectum. The tube is about as wide as a finger. Your doctor may also take *biopsies* (tissue samples) or remove *polyps* (growths).

The colonoscopy takes about 30 to 45 minutes. Your appointment may last longer to allow time to prepare and recover.

Afterward, your doctor may talk with you about the results. If your results are not ready right away, we will tell you when you can expect to receive them.

## Questions?

Your questions are important. Please call if you have questions or concerns. Weekdays between 8 a.m. and 5 p.m., call the clinic where your colonoscopy is scheduled. After hours and on weekends and holidays, call the Community Care Line at Harborview, 206.744.2500.

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 05/2012, 12/2015, 04/2016, 06/2016, 03/2018
Clinician Review: 03/2018
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu